ፓኖራማ ቁጥር 99

የትዝብት አድማስ

ኅዳር 1 ቀን 2003 ዓም

## የጋራ ራዕይ የሌለው ተቃዋሚ ፥ የአምባገነን ሥርዓት ሰለባ ሆኖ ይቀራል

በወያኔ ዘረኛ ቡድን የተመሰረተው አምባገነን የጎጠኞች ሥርዓት በኢትዮጵያ ከተንሰራፋ ይኸው አስራ ዘጠኝ ዓመታትን ጨርሶ ወደ ሀያኛው ዓመት ገብቷል። በዘመን አቆጣጠር ሲመደብ፥ ወደ ሩብ ምዕተ-ዓመት እየተጠጋ ነው ። ይህ ዘመን በኢትዮጵያ ታሪክ ዜና መዋዕል የመከራ፥ የውርደት ፥ የሀፍረት፥ የጥፋት፥ የጥቃት፥ የመቆራረስ ፥ የመጥበብና የመከፈል ታሪክን መዝግቦ አስቀምጧል ።የሀገሪቱ ዳር -ድንበር ተደፍሯል፥ የነበረው የቆዳ ስፋቷ ተጨረማምቷል ።የረሃብና የችግር፥ የእስራትና ግድያ፥ የመከራና የጭቆና፥የስደትና የመንከራተት ዘመን ሆኗል ። ለወያኔና ለወገኖቹ ወርቃማው ዘመን ሲባል ፥ ለቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ ዘመነ-ፍዳ ፥ ዘመነ-መርገም ሆኗል ። የሀገራችን አኩሪ ታሪኳ እየተዋረደ በአሳፋሪ ድርጊትና ሁኔታ እየተለወጠ በመሄድ ላይ ይገኛል ። ታፍሮና ተከብሮ የቆየው የሕዝቡ ባኅልና እሴት፥በአልባሌና ርካሽ የባዕዳን ባኅልና መጥፎ ልምድ በመለወጥ ላይ ነው ። ሀገሪቱም የባዕዳን መጨፈሪያ፥ የሀብት መዝረፊያ፥ ያሻቸውን የሚፈጽሙባት ምድር ሆናለች። የኢትዮጵያ ለም መሬቶችና የከርሰ ምድሯ ሀብቶች ሁሉ ለባዕዳን በሀራጅ እየተቸበቸቡ ነው። ለዚህ ጨረታ ሽቅድድም፥ቻይና፥ ህንድ፥ ግብፅ፣ሳውዲ አረቢያና ኳታር ግንባር ቀደሙን ቦታ ይዘዋል ። ባለቤት የሌላት ሀገር ሆና ስላገኟት ፥ ለብዙ ጊዜ ሲመኙት የነበረው ኅልም እውን ሆኖላቸዋል ።

የሕዝብ ጥቅም ተቆርቋሪ÷ የሀገር ነፃነት ቀናዒ ÷ የብሔራዊ ክብር አስጠባቂ መንግሥት ባለመኖሩ ሀገራችን ኢትዮጵያ የወያኔዎች ጠባብ ዓላማ ማስፈፀሚያ ሀገር ሆናለች :: ከአንድ ጎጥ የተውጣጡ የወገን ጠላቶች ÷ ከባዕዳን ባላንጣዎች በበለጠ መንገድ ሀገሪቷን እየጎዷት ይገኛሉ :: ሀገር አጥፍቶ መጥፋት የማነኛው አምባገነን ሥርዓት የጋራ ባኅርዩ ስለ ሆነ ወያኔዎቹ በመጨረሻ ሰዓት ÷ኢትዮጵያን አጥፍተው እንደሚጠፉ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግልፅ ከሆነለት ቆይቷል :: ሀገሩን ከዚህ ጥፋት ለማዳን ምን መደረግ እንዳለበት ደግሞ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ስውር አይደለም :: በሁለንተናዊ መንገድ ታግሎ ወያኔን ማስወገድ የሁሉም ዜጋ ዕምነትና ፍላጎት ብቻ ሳይሆን የመጀመሪያው የትግል አጀንዳው መሆኑን በሚገባ ተረድቶታል :: አምባገነን ሥርዓትን ለመታገል ደግሞ የጅምላ ስብስብ ሳይሆን አስፈላጊውን ድርጅታዊ መስፈርት አሟልቶ መደራጀትን ይጠይቃል :: ተደራጅቶ መታገል ብቻ ሳይሆን ÷ ደርጅቶና ተጠናክሮ መገኘት ÷ የአምባገነን ሥርዓትን ዕድሜ ለማሳጠር ፍቱን መድህኒት ነበር:: ያ ግን እስካሁን እውን ሊሆን አልቻለም :: ለምን ?

ለአለፉት አስራ ዘጠኝ ዓመታት ኢትዮጵያ ሀገራችን በዘመነ -ፍዳ ውስጥ ያለች መሆኗን እንኳንስ ዜጓቿ ÷ አስተዋይ ኅሊና ያለው የዓለም ሕዝብ ሳይቀር የሚያውቀው ሀቅ ነው :: ይህ የዘመነ-ፍዳ ክስተት ከደርግ ሥርዓት የቀጠለ በመሆኑ ÷ የሀገራችንን የመከራ ገመድ በአስከፊ ሁኔታ እንዲራዘም አድርጎታል :: በዚህም ደርግ ለወያኔ ከፍተኛ ሥራ ሰርቶለታል :: የሀገራችን ባዕዳን ጠላቶች ለወያኔ ወደ ሥልጣን መምጣት ካደረጉለት ርዳታና ትብብር በበለጠ ደርግም ለወያኔ በከፍተኛ ደረጃ ስለተባበረው ÷ ዘለዓለማዊ ባለውለታው ሆነዋል :: ለዚህም ሁለት መሠረታዊና የታሪክ ሀቆችን መጥቀስ ይቻላል ::

1ኛ. ደርግ በአብዮት ስም÷ የኢትዮጵያን አርበኞች÷ለሀገራቸው ከፍተኛ ውለታ የከፈሉትን ጀግኖችን ÷ሀገር ወዳድ ዜጎችን ÷ ተራማጅ ምሁራንንና ወጣቶችን ÷ ሊቃውንት አዛውንትን÷ የሐይማኖት መሪዎችን÷ አርሶ አደሮችንና ሠረተኞችን ሁሉ ሳይቀር ጨፈጨፈለት÷ መተረለት :: ሀገሪቱንም ሰው- አልባ አድርጎ ባዶዋን አስቀረለት:: ያለ ተቆርቋሪና ተሟጋች ሀገርና ሕዝብ እንዲያገኝ ዕድል ሰጠው :: ወያኔ በባዶ ቤት ሰተት ብሎ ለመግባት እንዲችል ሁሉንም አመቻቸለት:: የደርግ መሪዎችም ሀገሪቱን ለወያኔ እስከ ወርቅ ማዕደኗ አስረክበውት ሸሹ :: የሀገሪቱንም ብሔራዊ ምሥጢሮች እንዳለ አስረክበውት ጠፉ :: ለወያኔ ÷ ከደርግ የበለጠ ባለውለታ የለውም !

2ኛ. ደርግ ÷የኢትዮጵያን ከፍተኛ የመከላከያ ሠራዊት አዛዥ መኮንኖችን እንደ ጭዳ አረደለት :: በሀገሪቱ ሀብት የተማሩትን የጦር መኮንኖችና ባለሙያዎች ረሸነለት :: በሀገር ፍቅር ተወዳዳሪ ያልነበረውን የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል አፈራረሰለት ::

በቢሊዮን የሚገመት የሀገሪቱ ሀብት የፈሰሰበትን የጦር መሳሪያ ለወያኔ አስረክቦት ሄደ ። ይህን በደል ልብ ብለህ አስታውስ ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ !

ከዚህ በኋላ ለወያኔና ለኢትዮጵያ ጠላቶች ሁሉም ነገር ተመቻቸላቸው ። ወያኔና ተባባሪዎቹ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ሀብት ለመዝረፍ መልካም ዕድል አጋጠማቸው ። የኢትዮጵያ ሕዝብም ዐይኑ እያየ ፥ ጆሮው እየሰማ በሀገሩ ላይ የሚፈፀምበትን ብሔራዊ ወንጀል ለመከላከል ቀርቶ፥ ከወንጀሉ ለማምለጥ እንኳ ሳይቻለው ቀረ ። ለዚህም ዋናው ምክንያት፥ የጋራ ብሔራዊ ራዕይ ያለው የተጠናከረና የተባበረ ተቃዋሚ ኃይል የሌለ ለመሆኑ ማንም ሊከራከር አይችልም ። ለአለፉት አስራ ዘጠኝ ዓመታት ፥ወያኔን በተባበረ መልክ ተደራጅቶ ለመቃወም የሚያስችል የተቃዋሚ ድርጅቶች ኅብረት መፈጠር አስፈላጊና ወቅታዊ መሆኑ ታምኖበት፥ የሚከተሉት ሙከራዎች ተደረገው እንደ ነበር የታወቀ ነው።

1ኛ. በመጀመሪያ አምስት ድርጅቶችን የያዘ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት (ኢዴኃቅ ) ተመሠረተ ።

2ኛ. ፓሪስ አንድና ፓሪስ ሁለት የሚባሉ ሁለት የኅብረት ሙከራዎች ተደረጉ ።

3ኛ. የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ኅብረት (ኢተፖድኅ) በሚልም ተሞከረ ።

4ኛ. የአማራጭ ኃይሎች የሚል ስያሜን በመያዝ አዲስ አበባ በግዮን ሆቴል ሌላ የኅብረት ስብሰባ ተካሄደ ።

5ኛ. ከሁሉም በላይ ብዙ ጊዜ፥ጉልበትና ገንዘብ በመውሰድ ከፍተኛ ሙከራ የተደረገበት፥ አስራ ስድስት ድርጅቶችን ያካተተ ፥ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ( ኢዴኃኅ ) እንዲመጣ ተደረገ ።

ከላይ እንዳመጣጣቸው በጊዜ ቀመር የሰፈሩት ሙከራዎች ለትግሉ አስተዋፅዖ ያስደረጉ ቢሆንም፥ በሙሉ የታለመውን ግብ ሳይመቱ ቀሩ ። አንዳንዶቹማ ፥ እንዲያውም የተፈረመባቸው ቀለም ከመድረቁ በፊት ነበር የውሃ ሽታ ሆነው ያረፉት! የእያንዳንዳቸውን የታሪክ ሂደትና የአከሳሰማቸውን ምክንያት ለመዘርዘር የዚህ ሐተታ ዓላማ ስላይደለ ወደዚያ አናተኩርም ። የታሪክ ታዛቢዎችና ፥ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ትግል ዜና - መዋዕል የሚከታተሉ ዜጎች ትክክለኛውን ነገር እየመዘገቡት እንደሆነ ግን ይታመናል ።

በእኛ ዕምነት÷ ጠንካራ የተቃዋሚ ኃይሎች ኅብረት ለመፍጠር ከሚያስችሉት ዋና ዋና መሠረቶች ቀዳሚው÷ የጋራ ብሔራዊ ራዕይ መኖር ነው እንላለን ። እስካሁን ይህ የጋራ ብሔራዊ ራዕይ አለመኖር÷ ጠንካራ የተቃዋሚ ኃይል ኅብረት እንዳይፈጠር የራሱን አስተዋፅዖ አድርጓል ማለት የሚቻል ይመስለናል ። ይህን የጋራ ብሔራዊ ራዕይ ማጣት ጠንካራ የተቃዋሚ ኃይል እንዳይፈጠር ዋናው ምክንያት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ÷ የሚከተሉት ጉዳዮችም ቀዳሚ ብሔራዊ አጀንዳ ከመሆን የሚነፈጋቸው አይሆኑም ።

1ኛ. ማነኛውም ድርጅት ወደ ኅብረት ጉባዔ ለመሄድ ከመዘጋጀቱ በፊት÷ የስብሰባው አጀንዳ÷ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ማዕከል ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት ።

2ኛ. ይህ ማለት ÷ የኢትዮጵያ ኅልውና÷ የግዛቷ ልዕልና ÷በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የዜጎቿ ነፃነትና አንድነት÷ እንዲሁም ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ማለታችን ነው ።

3ኛ. በተራ ቁጥር አንድና ሁለት የሰፈሩትን መሠረታዊ ጉዳዮች አምኖና ተዘጋጅቶ መገኘት÷ የጋራ ብሔራዊ ራዕይ ለመኖር÷ የመጀመሪያው ርምጃ ነው። ይህ ደግሞ ለኢሕአፓ አልፋና ኦሜጋ ነው ። አይከፍሉ መሥዋዕት እየከፈለ የታገለበት ! አሁንም የሚታገልበት ብሔራዊ ራዕዩ ነው !

4ኛ. የድርጅትን መሠረታዊ መስፈርቶች አሟልቶ መገኘት÷ ለኅብረት ትግል ወሳኝ መሆኑ ሁሉም ሊገነዘበው ይገባል። የጉባዔን ድግስ ለመቋደስ ሲባል ብቻ የሚደረግ ሙከራ ሁሉ እስካሁን ፋይዳ አላመጣም ።

5ኛ. የጋራ ብሔራዊ ራዕይ ያለው ኃይል መኖር÷ ቢያንስ ሦስት ዐበይት ጠቀሚታዎችን ሊያስገኝ ይችላል ።

ሀ ) ያልተቋረጠና ያልተቆጠበ ሕዝባዊ ዕምነትና ድጋፍ ያገኛል።

ለ ) የአምባገነን ሥርዓት ሰለባ ከመሆን ይድናል። ይኸንንም ካደረገ ለቆመለት ሕዝብና ሀገር መከታ ይሆናል ።

ሐ ) በራሱ ኃይል ተማምኖ የሕዝብንም ሁለንተናዊ ድጋፍ አግኝቶ ስለሚታገል የአምባገነኖችን ዕድሜ ባጭር ይቀጫል ።

ወያኔን እስከ አስከፊው ሥርዓቱ ለማንበርከክ ፥ ለአለፉት አስራ ዘጠኝ ዓመታት የኾነውን ሂደት በሚገባ መርምሮ ፥ በአዲስ ስልት ፥ ፈርጀ- ብዙ ትግል ማካሄድ ወቅታዊ የሕዝብ ጥያቄና ሀገሪቱም የምተጠብቀው ብሔራዊ ጥሪ ነው ። <u>ይኽንን ሕዝባዊ ጥያቄና ብሔራዊ ጥሪ ለመመለስ የሚቻለው ደግሞ፥ የጋራ ብሔራዊ ራዕይ ያለው ኃይል ሲፈጠር ብቻ ነው ።</u> ይህንን ዕውን ለማድረግ ይቻል ዘንድ ኢሕአፓ ህልውና ያላቸውን ኢትዮጵያዊ ድርጅቶችን ለውይይት መጋበዙ የሚታወስ ነው ። የወያኔ ሥርዓት ሰለባ የሆኑት ክፍሎች አበክረው እንዲያስቡበት ጥሪያችንን ዳግም እናስተላልፋለን ።